IBO IB DIPLOMA PROGRAMME
PROGRAMME DU DIPLÔME DU BI
PROGRAMA DEL DIPLOMA DEL BI

M06/1/A1AMH/SP2/AMH/TZ0/XX

22060016

**AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 2**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 2**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 2**

Tuesday 23 May 2006 (afternoon)
Mardi 23 mai 2006 (après-midi)
Martes 23 de mayo de 2006 (tarde)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the Part 3 works you have studied. You may include in your answer a discussion of a Part 2 work of the same genre if relevant. Answers which are not based on a discussion of at least two Part 3 works will not score high marks.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Traitez un seul sujet de composition. Vous devez baser votre réponse sur au moins deux des œuvres de la 3e partie que vous avez étudiées. Le cas échéant, vous pouvez inclure dans votre réponse une discussion sur une œuvre du même genre littéraire étudiée dans la 2e partie du programme. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la 3e partie n'obtiendront pas une note élevée.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Elija un tema de redacción. Su respuesta deberá basarse en al menos dos de las obras estudiadas en la Parte 3. Se podrán hacer comentarios sobre una obra de la Parte 2 del mismo género, si fuera necesario. Las respuestas que no incluyan una discusión sobre al menos dos obras de la Parte 3 no recibirán notas altas.

***ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ሀተታ ፃፍ(ፃፊ)፡፡ መልስህ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ መመስረት አለበት፡፡ በክፍል ሁለት ስር ከሚገኝ አንድ ተመሳሳይ የስነጽሁፍ ዘርፍ ማጣቀሻ ማስገባት ይፈቀዳል፡፡ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ ያልተመሰረተ መልስ ከፍተኛ ነጥብ አያስገኝም፡፡***

**ድራማ**

1. ተከታዩን

(ሀ) የአንድ ቴአትር ውበት የሚለካው በትእይንቱ ሃይል ነው፡፡ ደህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ድራማዎች በማወዳደር ግለጽ፡፡

ወይም ቀጣዩን ምረጥ፡፡

(ለ) የአንድ ተውኔት ምልልስ በገፀባህሪያቱ መካከል ያለውን ግጭት በማሳየት የተውኔቱን ድራማዊ ገጽታ ያጎላል፡፡ ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ፀሃፊዎቹ ይህንን ያቀረቡበትን መንገድ አሳይ፡፡

**ረጅም ልቦለድ**

2. ተከታዩን

(ሀ) ረጅም ልቦለድ በማንኛውም መመዘኛ ታሪክ ነው፡፡ ካነበብካቸው ስራዎች መካከል ይህንን ሃሳብ እንድትደግፍ ወይም እንድትቃወም ያደረጉህን ቢያንስ ሁለት ስራዎች ትልም (ፕሎት) አነፃፀር፡፡

ወይም ቀጣዩን ምረጥ፡፡

(ለ) የረጅም ልቦለድ ገፀባህርያት የሚያከናውኗቸው ድርጊቶች ሁሉ አሳማኝ መነሻ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ መልስህ ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት የሚጠቅስ ይሁን፡፡

**ስነግጥም**

3. ተከታዩን

(ሀ) የግጥም ዋነኛ መለያ ባህሪ አንድን ጉዳይ ግልጥልጥ አድርጎ የማሳየት ሀይሉ ነው፡፡ ያጠናሃቸውን ሁለት ግጥሞች በማወዳደር ግጥሞቹ ምን እንዳሳዩህና በምን መንገድ እንደቀረቡ አስረዳ፡፡

ወይም ቀጣዩን ምረጥ፡፡

(ለ) ስነግጥም በምናብና በስሜት አማካኝነት የህይወት ገጽታዎች ትርጉም የሚገለጽበት ጥበብ ነው፡፡ በዚህ ሃሳብ ምን ያህል ትስማማለህ? መልስህ የሁለት ገጣምያንን ቢያንስ ሁለት ስራዎች ጭብጥና ስልት የሚያወዳደር ይሁን፡፡

**ዝርው (ከአጭርና ረጅም ልቦለድ ውጪ)**

4. ተከታዩን

(ሀ) የአንድ ዝርው ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) ፀሃፊ ስለራሱና ስለሰው ልጆች የህይወት ልምድ በጽሁፉ ይገልፃል:: ይህ ሃሳብ ትክክለኛ መሆኑን ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማወዳደር አስረዳ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) አንድ ዝርው ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) የሚያቀርበው ጉዳይ በጽሁፉ  ውስጥ በበቂና በተሙዋላ ሁኔታ መቅረብ የሚችል መሆን አለበት:: ያነበብካቸውን ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ሃሳቡን አስረዳ::

**አጭር ልቦለድ**

5. ተከታዩን

(ሀ) በአጭር ልቦለድ ጡዘት (ክላይማክስ) የአጭር ልቦለዱ ግጭት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚደርስበት ነው:: ያጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች ጡዘቶች አቀራረብ ይህንን ሃሳብ እንደሚደግፍ ወይም እንደማይደግፍ አሳይ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) የአጭር ልቦለድ ገፀባህሪ በተለያዩ መንገዶች እራሱን እንዲገልጽ መደረግ አለበት:: ያጠናሃቸው ሶስት አጭር ልቦለዶች ደራስያን የገባህሪያቶቻቸውን ትክክለኛ ማንነት ያሳዩበትን መንገድ አወዳድር::

**ሁለገብ (አጠቃላይ)**

**6.** ከሚከተሉት አንዱን መርጠህ መልስ(ሽ)።

(ሀ) ስነጽሁፍ ሁኔታዎችን የመረዳትና ከሌሎች ጋር የመግባባት አቅማችንን በማጎልበት ህይወታችንን የተሟላ ያደርጋል። ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር መልስ ስጥ።

ወይም

(ለ) ስነጽሁፍ ሰዎች በፍላጎት የሚያነብዋቸው መጽሀፍት ስብስብ ነው። ካጠናሃቸው ስራዎች አንፃር በዚህ ሀሳብ ትስማማለህ?

ወይም

(ሐ) የአንድ ታላቅ ስነጽሁፍ ስራ ዋነኛ መለያው አንድን ልዩና አዲስ ጉዳይ በልዩና አዲስ መንገድ ማቅረብ መቻሉ ነው። አንተ በተለየ ቅድሚያ የምትሰጠው ለየትኛው መንገድ ነው?

ወይም

(መ) ስነጽሁፍ የሚመነጨው ከህይወት ውስጥ ሲሆን የሚመገበውም ህይወትን ነው። ይህንን ሃሳብ በሁለት ስራዎች ምሳሌነት አብራራ።